# <u>ጆሮ ያለው ይስማ</u>

አገር ሲፈራርስ ፣ ተደፍሮ ፣ ዳር ድንበር
ፍትህ ፣ አይኗ ጠፍቶ ፣ ጭራሽ ስትታወር
ዜጋ ፣ ባገሩ ላይ ፣ ሲሳደድ ሲታሰር
አለፍርድ ሲሞት ፣ ሲገደል ሲመተር
ለመኖር ተስኖት ፣ ጥሎ ፣ ሲሄድ ካገር
አስር ቢንፈራገጥ ፣ መብቱን ለማስከበር
ትግል ፣ በዘር ሆኖ ፣ የዘር ግንድ ፣ ሲቋጠር
በደል ፣ በረታ እንጂ ፣ አልቀለለም ቀንበር
ያመጣው ፣ ለውጥ የለም ፣ ከመከራ በቀር
ፋሽስትን ከማገዝ ፣ እየዋል እያደር
ሂሳብ ሲወራረድ ፣ በጎጥና መንደር ።

    ህዝብ  በየፊናው ፣ ከተበታተነ
    በቋንቋ ፣ ባገር ልጅ ፣ መርጦ ከወገነ
    አገር ፣ ማለት ቀርቶ ፣ መንደር ከገነነ
    የጎጥና ፣ ጎሳ ፣ ስካር ካልሰከነ
    ኢትዮጵያዊነትን ፣ ገሎ ካመከነ
    የፋሽስት ሰለባ ፣ ጭዳ እየተሆነ
    ሁሉንም ያጠፋል ፣ በተራ እያደነ ።

አገሬው በሙሉ ፣ መብቱ እየተቀማ
ባራቱም ማዕዘን ፣ ወገን እየደማ
በጎሳ ስብስብ ፣ ሌላን ማግለልማ
ከኪሳራ በቀር ፣ ሲያተርፍ አልተሰማ
ለሁሉም የሚበጅ ፣ ሁሉን የሚያስማማ
ህብረ ብሄራዊ ፣ የአንድነት ግርማ
ኢትዮጵያዊነት ነው ፣ ጆሮ ያለው ይስማ ።

ታዛቢው … March 8, 2010